Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL

# የልዩ አመጋገብ መግለጫ ቅጽ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የምግብ እና የተመጣጠነ አመጋገብ አገልግሎቶች መምሪያ

Department of Food & Nutrition Services MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Gaithersburg, Maryland 20879

## ሰክሽን A—በወላጅ/አሳዳጊ መሞላት አለበት።

የተማሪ ስም ______________ የተማሪ መታወቂያ ቁጥር ______________ የክፍል ደረጃ ______

የትምህርት ቤት ስም ______________ የትምህርት ቤት ቁጥር ______

የአስተማሪ ስም ______________

የወላጅ/የአሳዳጊ ስም (ይጻፉ) ______________

የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ ______________

ኢ-ሜይል ______________

የስልክ ቁጥር ______-______-______ ቀን ____/____/____

## ሰክሽን B— የስቴት ፈቃድ ባለው የጤና ባለሙያ ወይም ፍቃድ ባለው የምግብ ባለሙያ መሞላት አለበት

ተማሪው(ዋ) የምግብ አለርጂ አለው/አላት? ❏ አዎ ❏ የለውም/የላትም

አዎን ከሆነ፥ እባክዎን ከዚህ በታች ካለው ዝርዝር ውስጥ የማይስማማውን አይነት ምግብ ይግለጹ

- ❏ ስንዴ
- ❏ የወተት ተዋፅኦ
  - ❏ ወተት ያለበት የተጋገረ ምግብ ችግር የለውም (ለምሳሌ፡- ፓንኬክ)
  - ❏ እርጎ ችግር የለውም።
  - ❏ አይብ/ቺዝ ይስማማዋል/ይስማማታል።
- ❏ ለውዝ
- ❏ እንቁላል
  - ❏ እንቁላል ያለበት የተጋገረ ምግብ ችግር የለውም (ለምሳሌ፡- ፓንኬክ)
- ❏ አኩሪ አተር
  - ❏ የአኩሪ አተር ዘይት ይስማማዋል/ይስማማታል።
- ❏ ኦቾሎኒ
- ❏ ዓሣ
- ❏ ሼልፊሽ
- ❏ ሰሊጥ

ሌላ፡ ______________

ተማሪው(ዋ) ሌላ ልዩ የአመጋገብ ሁኔታ ወይም የምግብ ፍላጎቶች አሉ(ሏ)ት? ❏ አዎ ❏ የለውም/የላትም

እባክዎን የተለየ የምግብ አዘገጃጀት ማለት(የተጣራ)፣ ሴሊያክ በሽታ፣ የስኳር በሽታ፣ ወዘተ የመሳሰሉ ልዩ የምግብ/የአመጋገብ ፍላጎቶች ካሉ(ሏ)ት ይግለጹ።

______________

______________

ልጅዎ በትምህርት ቤት የምግብ ፕሮግራም ውስጥ ቁርስ እና/ወይም ምሳ ይሳተፋል? ❏ አዎ ❏ አይሳተፍም/አትሳተፍም
አዎ ከሆነ፣ እባክዎን በምን ያህል ጊዜ እንደሆነ ይግለጹ (ለምሳሌ፡- በየቀኑ፣ በሳምንት የተወሰኑ ቀናት፣ አልፎ አልፎ): ______________

______________

ከላይ የተጠቀሰ(ች)ው ተማሪ ከዚህ በላይ በተገለፀው መሠረት ልዩ የትምህርት ቤት ምግብ የሚያስፈልገው/የሚያስፈልጋት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

የስቴት ፈቃድ ያለው የጤና ባለሙያ ወይም ሠርተፊኬት ያለው የስርአተ ምግብ ባለሙያ ብቻ ከዚህ በላይ ያለውን መረጃ በፊርማ ማረጋገጥ ይችላል።

ስም (ይጻፉ) ______________ የቢሮ ስልክ ቁጥር ______-______-______

ፊርማ ______________ ቀን ____/____/____

# የልዩ ምግብ ፍላጎት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
የምግብ እና የተመጣጠነ አመጋገብ አገልግሎቶች መምሪያ
Department of Food & Nutrition Services
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Gaithersburg, Maryland 20879

**የበፊት ታሪክ መረጃ፦**

የአካል ጉዳተኝነት ያለባቸው አሜሪካኖች ህግ (ADA) ላይ አብዛኞቹ የአካል እና የአዕምሮ እክሎች የአካል ጉዳተኝነት መሆኑ ተገልጿል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የምግብ እና የተመጣጠነ ምግብ አገልግሎት መምሪያ (DFNS) በትምህርት ቤት የምግብ ፕሮግራሞች ላይ የመሳተፍ እና የፕሮግራም ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት እኩል የተደራሽነት እድል ለማረጋገጥ ከወላጆች እና ከሌሎች የሚመለከታቸው የዲስትሪክት ሰራተኞች ጋር በትብብር ይሰራል። ትምህርት ቤቶች የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ምግብ በሚስማማቸው አይነት ማስተካከል አለባቸው። ይህ ምግብን የማስተካከል ሁኔታ የሚከናወነው በተማሪዎቹ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የሚቀርቡት ጥያቄዎች ፈቃድ ካለው የጤና ባለሙያ በጽሁፍ መግለጫ ሲደገፍ ብቻ ነው — የልዩ ምግብ ፍላጎት መግለጫ ቅጽ (ገጽ 1)። ትምህርት ቤቶች የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አመጋገባቸው ላይ ተጽእኖ ለሚፈጥርባቸው ሁኔታዎች የምግብ ማስተካከያ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። አጠቃላይ የጤና ስጋቶች፣ ለምሳሌ ለተማሪው(ዋ) የተሻለ ነው ብሎ ወላጅ ስለሚያምን አንድ ተማሪ ከግሉተን-ነጻ ምግብን እንዲመገብ የሚፈልጉ ከሆነ፣ የአካል ጉዳተኛ ስላልሆነ(ች) ልጅ ልዩ የምግብ ዝግጅት አይደረግላቸውም። DFNS በአመጋገብ ፕሮግራም አዘገጃጀት መደበኛ የአካል ጉዳተኞችን ለማስተናገድ የምግብ ዝግጅት እቅድ ይኖራል። አብዛኛው የአካል ጉዳተኞች በመደበኛው የስርዓተ ምግብ ዝግጅት መስተናገድ ይችላሉ። DFNS የተጠየቀውን የተለየ የምግብ ለውጥ ወይም ሌላ ማሻሻያ እንዲያቀርብ አይጠበቅበትም፥ ነገር ግን ምክንያታዊ የሆነ የምግብ ለውጥ የተማሪን የአካል ጉዳት የሚረዳ እና እኩል በፕሮግራሙ ውስጥ የመሳተፍ ወይም የመጠቀም እድል ይሰጣል።

የአኩሪ አተር ወተት ለመጠየቅ የልዩ ምግብ ፍላጎት (SDN) ቅጽ ማቅረብ አያስፈልግም። የአኩሪ አተር ወተት በሁሉም ትምህርት ቤቶች ይገኛል። ነገር ግን፣ ልጅዎ ከአኩሪ አተር ሌላ የወተት አማራጭ ከፈለገ(ች)፣ SDN ቅጽ ሞልተው ማቅረብ አለብዎት።

**የአፈጻፀም ሒደት**

አንድ ጊዜ የተለየ የምግብ ፍላጎት መግለጫ ቅጽ ከተሞላ በኋላ፣ ቅጹ እንዲደርሳቸው DFNSOffice@mcpsmd.org DFNS central office የዋና ጽሕፈት ቤት ሠራተኛ በኢሜይል ይላካል። የልዩ አመጋገብ ፍላጎት መግለጫ ቅጽ ተሞልቶ ከቀረበ፣ የስቴት ፈቃድ ያለው የጤና ባለሙያ ወይም ሠርተፊኬት ያለው የምግብ ባለሙያ ፊርማ ካለው፣ ቅጹ በተማሪው(ዋ) የምግብ ዝርዝር ውስጥ መግባቱን ለማረጋገጥ ወደ DFNS የተመዘገቡ የምግብ ባለሙያዎች ይተላለፋል። DFNS የተመዘገበ የምግብ ባለሙያ እና ወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች) በምግብ ዝርዝር እቅዱ ላይ ከተስማሙ በኋላ ሰራተኞች እንዲያውቁት እና አስፈላጊ ከሆነም ምግብ መታዘዙን ለማረጋገጥ እቅዱ ወደ ትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘር ይላካል። የምግብ ዝርዝሩ መለጠፍ ያለበት በትምህርት ቤቱ ካፊቴሪያ ውስጥ በተገቢ ቦታ ላይ ሲሆን የካፊቴሪያው አስተዳዳሪ እና ሰራተኞች የሚደርሱበት ቦታ መሆን አለበት። አንዳንድ ተማሪዎች የተዘጋጀላቸው ምግብ እንዳይበከል ታሽጎ እንዲቀመጥላቸው ሊፈልጉ ይችላሉ። እባክዎ ያስተውሉ፦ የልዩ አመጋገብ ፍላጎት መግለጫ ቅጽ በተናጥል፣ ወይም ከ 504 ፕላን በተጨማሪ፣ ወይም ካለው 504 ፕላን 525-14 በተጨማሪ (ለተማሪው(ዋ) የምግብ አለርጂ/አናፊላክሲስ የድንገተኛ አደጋ ጊዜ እንክብካቤ ጥቅም ላይ ይውላል)።